**የሱዳን መንግስት የወያኔን መንግሥት በትጥቅ ከሚታገሉ ሃይሎች ጋር ግንኙነት አላቸው የሚባሉ ከ24 በላይ ኢትዮጵያውያንን ይዞ ማሰሩ ታወቀ። ህጋዊ የመኖሪያ ፈቃድ የላቸውም የተባሉ በሺዎች የሚቆጠሩ ኢትዮጵያውያንንም በሃይል ከአገር ለማባረርም ዝግጅቱ ተጠናቋል።**

**ሀምሌ 11 ቀን 1999ዓ.ም**

**ገረመው ሃይሉ**

የሱዳን መንግስት ብዛት ያላቸው የኢትዮጵያ ተቃዋሚ ሃይሎች አባላትን ከሃምሌ 1999ዓ.ም.መጀመሪያ ጀምሮ ማሰሩ ታውቋል። ኢትዮጵያውያኑ የተያዙት ከሚኖሩበት ቤት፤ ከሚሰሩበት ቦታና ከሚያዘወትሩበት ምግብ ቤት እየታደኑ ነው። እስካሁን ባለው መረጃ መሰረት የታሰሩት ኢትዮጵያውያን የወያኔን ስርአት በሃይል ለመጣል ከሚፈልጉ ሃይሎች ጋር ግንኙነት አላቸው ተብለው የሚጠረጠሩ ናቸው። ውስጥ አዋቂዎች እንደሚሉት ከሆነ በጠቅላላ ከሚፈለጉት 35 ሰዎች 24ቱን ይዞ ማሰሩን ከነዚህም ውስጥ 11ዱ ከኦነግ ጋር የተቀሩት ደግሞ የአርበኞች ግንባር የሚባለው ሃይል ግንኙነት አላችሁ በሚል ጥርጣሬ  መሆኑ ታውቋል። እስካሁን በተደረገው ሙከራ የሱዳን መንግስት ኢትዮጵያውያኑን የት ቦታና በምን ሁኔታ እንዳሰራቸው በውል ማወቅ አልተቻለም። ከተያዙ በኋላ የት እንዳሉ ከማይታወቁት ውስጥ  የተወሰኑትን በሚስጥር ለወያኔ አሰረክቦ ይሆናል የሚል ስጋትም አለ። የተባበሩት መንግስታት የስደተኞች ጉዳይ ከተኛ ኮሚሽን ባልደረቦች ጉዳዩን እየተከታተሉ መሆኑን ከመግለጽ ያለፈ መረጃ ለመስጠት ፈቃደኞች አልሆኑም።

ረቡእ አመሻሹ ላይ በተገኘው መረጃ መሰረት በነዚህ ኢትዮጵያውያን ጉዳይ ላይ የሱዳን የስደተኞች ኮሚሽን፤ የሱዳን የውጭ ጉዳይ ደህነት መስሪያ ቤትና የተባበሩት መንግስታት የስደተኞች ከፍተኛ ኮሚሽን ከፍተኛ ባለስልጣናትና የሶስትዮሽ ስብሰባ ሀሙስ ሃምሌ 12ቀን 1999ዓ.ም እንደሚቀመጡ ታውቋል። አለም አቀፉ የምህረት ጠያቂ ድርጅት /የአምነስቲ ኢንተርናሽናል/ ጉዳዩን እይተከታተለ መሆኑን ታውቋል።

የሱዳን መንግስት ከወያኔ ጋር ባለው የጠበቀ ወዳጅነት የተንሳ አለማቀፍ ውሎችን በመጣስ በተድጋጋሚ ኢትዮጵያውያን የፖለቲካ ስደተኞችን አሳልፎ ለወያኔ መስጠቱ ይታወቃል።

**በሌላ በኩልም**
**ሱዳን በብዙ መቶዎች የሚቆጠሩ  ህጋዊ የመኖሪያ ፈቃድ የሌላቸውን ኢትዮጵያውያንን ከአገሯ ለማባረር በዝግጅት ላይ መሆኗ ታውቋል።**

የሱዳን የጸጥታ ሰራተኞች ከሃምሌ አምስት እኩለ ሌሊት የጀመሩትን ኢትዮጵያውያን በሚያዘውትሯቸው ምግብ ቤቶች፣ ሻይቤቶች፤ እና መኖሪያ ግቢዎችን በሃይል በመውረር ህጋዊ መታወቂያ የሌላቸውን ኢትዮጵያውያን ማሰራቸውን ቀጥለዋል። ሺሻ በሚጨስባቸው፤ በህገወጥ መንገድ የሚገባው ጫት ይቃምባቸዋል በሚባሉና በድብቅ መጥጥ ይሸጥባቸዋል የተባሉ ቤቶች በፍተሻው ከፍተኛውን ትኩረት የሚደረግባቸው ቢሆንም የታሰሩት ጥረው ግረው የራሳቸውንና የቤተሰባቸውን ችግር ለመቅረፍ የሚሯሯጡ ናቸው ። ወደ ሺህ የሚጠጉ ኢትዮጵያውን በሙግረን፤

ኡምዱርማን፤ በባህሪና በአርከዊት በሚገኙ ፖሊስ ጣቢያዎች ታጉረው እንደሚገኙ ለማወቅ ሲቻል ብዙ ኢትዮጵያውያን በተያዙበት ወቅት ቤታቸው እንደተበረበረና በአንዳድ እስርቤቶችም ድብደባ እንደሚፈጸምባቸውም ለማወቅ ተችሏል።

ሁሉም የታሰሩት ኢትዮጵያውያውን ፍርድ ቤት የቀረቡ ሲሆን መታወቂያ የሌላቸው ሁሉ ከ5- 30 ቀናት በሚደርስ እስራትና ከ 50ሺ. እስከ 100ሺ. የሱዳን ፓውንድ ከተቀጡ በኋላ ከአገር እንዲባረሩ እንደተወሰነባቸው ለማወቅ ተችሏል።

ዘግይቶ ማምሻውን በተገኘው መረጃ መሰረት በመቶዎች የሚጠጉ የእስር ጊዜቸውን የጨረሱት ኢትዮጵያውያን ዛሬ ረቡእ ሀምሌ 11ቀን 1999 ዓ.ም ሊባረሩ በመኪና ተጭነው መንገድ ከጀመሩ በኋላ ወደ ነበሩበት እስቤት መመለሳቸው ታውቋል።

እነዚህ ህጋዊ የመኖሪያ መታወቂያ የላችሁም ተብለው በሱዳን ጸጥታ ሰራተኞች በቁጥጥር ስር የዋሉና ከሱዳን እንዲባረሩ የተፈረደባቸው ኢትዮጵያውያን በሶስት  የሚመደቡ ናቸው። አንደኛውና ከፍተኛ ቁጥር ያለው  ምድብ ለስራ ፍለጋ ህጋዊ በሆነ መንገድ ፓስፖርት አውጥተው አንድም በደላሎች አለያም በራሳቸው ወደ ሱዳን የገቡ ወጣት ሴቶች ናቸው። ሁለተኛው ምደብ ባለፉት ሁለት ሶስት አመታት የተሰደዱና የስደተኛ መታወቂያ የተነፈጉ የፖለቲካ ስደተኞች ሲሆኑ ሶስተኛው ምድብ ከብዙ አመታት በፊት በፖለቲካ ምክንያት የተሰደዱ ነገር ግን  በአንዱ ወይም በሌላው ምክንያት ህጋዊ መታወቂያ የሌላቸው ናችው።

ታዛቢዎች እንደሚሉት እንዲባረሩ የተፈረደባቸው ኢትዮጵያውያን ለአመታት ያፈሩትን ሃብትና ንበረት የመሰብሰብ ወይም ለአደራ የመስጠት እድል ሳያገኙ መሆኑ ከሁሉም የከፋው በደል ነው።

የሱዳን መንግስት መታወቂያ የሌላቸውንና ባለፉት ቅርብ አመታት ወደ ሱዳን  የገቡ የተወሰኑ ከተሜ ወጣት ኢትዮጵያውን ሴቶችን  የሽሪያን ህግ በመጣስ ይከሳል።

የሱዳን መንግስት ኢትዮያውያኑን የፖለቲካ ስደተኞችና መታወቂያ የሌላቸውን ኢትዮጵያውናን መያዝና ማሰር  የጀመረው የወያኔ መንግስት ለም የእርሻ መሬት ለሱዳን መስጠቱ ይፋ በሆነ ማግስት መሆኑ ወያኔና የሱዳን መንግስት የህዝቡን የትኩረት አቅጣጫ ለመቀየር ያቀነባበሩት ሳይሆን እንዳልቀረ  የሚናገሩም ብዙዎች ናቸው።